# SUN Bucks
# ቤተሰብዎን እንዴትመርዳትእንደሚችል ይወቁ!

SUN Bucks ትምህርት ቤቶች በሚዘጉበት በበጋ ወቅት ቤተሰቦች ምግብ እንዲገዙ ለመርዳት የተዘጋጀ የምግብ ግሮሰሪ ድጎማዎች ፕሮግራም ነው። ቤተሰቦች ለእያንዳንዱ መስፈርቱን ለሚያሟላ በትምህርት ዕድሜ ላይ ላለ ልጅ $120 ያገኛሉ። እነዚህን ጥቅማጥቅሞች የሚያገኙ ልጆች በሌላ የበጋ ወቅት የምግብፕሮግራሞች ላይ አሁንም መሳተፍይችላሉ።

## ልጄ ለSUN Bucks መስፈርቱን የሚያሟላ ነው?

ልጅዎ ለSUN Bucks ብቁ የሚሆነው ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ከተሟላ ነው፦

- ቤተሰብዎ ቀደም ሲል ለችግረኛ ቤተሰቦች በሚደረግ ጊዜያዊ እርዳታ (Temporary Assistance for Needy Families) ወይም በSNAP (Supplemental Nutrition Assistance Program, ተጨማሪ የአልሚ ምግብ እርዳታ ፕሮግራም) ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፍ ከሆነ እና የልጅዎ ዕድሜ ከ8 እስከ 18 ዓመት ከሆነ።
- ልጅዎ ብሔራዊየትምህርት ቤት የምሳ ፕሮግራም (National School Lunch Program) ወይም የትምህርት ቤት የቁርስ ፕሮግራም (School Breakfast Program) የሚያቀርብ ትምህርት ቤት የሚማር ከሆነ እና የቤተሰብዎ ገቢ ለነፃ ወይም ለቅናሽ ዋጋ የትምህርት ቤት ምግቦች የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ። ልጅዎ ለነፃ ወይም ለቅናሽ ዋጋ ምግቦች ብቁ መሆኑን ለማወቅ በልጅዎ ትምህርት ቤት የህጻናት አመጋገብ ብቁነት እና የትምህርት ጥቅማጥቅም (Child Nutrition Eligibility and Education Benefit application) ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ።

## ቤተሰቦች የSUN Bucks ጥቅማጥቅሞችን እንዴትያገኛሉ?

አብዛኛዎቹ መስፈርቱን የሚያሟሉ ቤተሰቦች በSUN Bucks ውስጥ በራስ-ሰር የሚመዘገቡ በመሆናቸው ማመልከቻ ማስገባት አያስፈልጋቸውም። እነዚህ ቤተሰቦች በጁን ወር የSUN Bucks ካርድ በፖስታ ይደርሳቸዋል።

በራስ-ሰር ያልተመዘገቡ ከሆነ፣ አሁንም በበጋው ወቅት ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ።

## SUN Bucks ለማግኘት እንዴትማመልከት እችላለሁ?

በእንግሊዝኛ ቋንቋ በኦንላይን ለማመልከት sunbucks.dshs.wa.govን ይጎብኙ። እንዲሁም የQR ኮዱን ስካን በማድረግ የተተረጎሙ የSUN Bucks ማመልከቻዎችን ማግኘት እና ኮፒውን ፕሪንት ማድረግ ይችላሉ።

የተጠናቀቁ ማመልከቻዎችን በሚከተለው አድራሻ ይላኩ፦
DSHS Customer Service Center
P.O. Box 11669
Tacoma, WA 98411-6699

ሲያመለክቱ፣ የልጅዎን ስም፣ ትምህርት ቤት፣ የልደት ቀን፣ አድራሻ፣ እና የቤተሰብዎን ገቢ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። ማመልከቻውን በሚያስገቡበት ጊዜ ሌላ ማንኛውንም ሰነድ ወይም መረጃ ማቅረብ አያስፈልግዎትም። እርስዎ ጥቅማጥቅሞች ከመሰጠታቸው በፊት ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ ሊኖርብዎት ይችላል።

ስለ SUN Bucks ጥቅማጥቅምዎ ጥያቄዎች አሉዎት? አድራሻዎን ማዘመንይፈልጋሉ?

በስልክ ቁጥር 833-543-3230 ወይም በTTY 800-833-6348 ለSUN Bucks የመገናኛ ማዕከል ይደውሉ።

Washington Office of Superintendent of
PUBLIC INSTRUCTION